# አመርታ



## የንግድና ኢንዱስትሪ ሴክተር
## ዜና መፅሔት





በደቡብ ኢንቨስት ለማድረግ
ለምትፈልጉ ልማታዊ ባለሀብቶች
በራችን ምንጊዜም ክፍት ነው:





**ኤዲተር**
አበበ ደንጋሞ

**አዘጋጆች**
የኔወርቅ ቁምላቸው
አስፋው ብርሃኑ

**ዲዛይንና ጽሕፈት**
ዓለምፀሃይ ሙሉጌታ

## ማውጫ

| | ገጽ |
|---|---|
| ርዕሰ አንቀጽ | 3 |
| ቢሮው የሚሰጣቸቸውን አገልግሎቶች በዌብ ሳይት ማሰራጨት ጀመረ | 5 |
| ለኮሚኒኬሽን የሥራ ሂደት ሠራተኞች የመሠረታዊ የአሰራር ሂደት ለውጥ ሥልጠና ተሰጠ | 7 |
| የክላስተር ግንባታ እየተጠናቀቀ ነው | 9 |
| ከሠሩ ይጠቀማሉ | 11 |
| ለባለሀብቱ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጠ | 15 |

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለሥራችንና ለቃላችን ታማኝ እንሁን፡

ክልላችንን ብሎም ሀገራችንን ከድህነት ለማውጣት ልማታዊ መንግሥት ያስቀመጠውን ፖሊሲና ስትራቴጂ ተግባራዊ ስናደረግ መሆኑን በተለያዩ የውይይት መድረኮች ሁላችንም ስንገልፅ ቆይተናል፡፡

ከኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካል ኢኮኖሚ አመለካከት ተላቀን ወደ ልማታዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚ አመለካከት ለመግባት የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት በሚያስችሉ ብዙ መድረኮች ላይ ተሳትፈናል፤ በተሳተፍንም ቁጥር ቃል መግባታችንና ከላይ የተገለፀውንም ሃሳብ ማንሳታችን የሚዘነጋ አይደለም፡፡ እርግጥ ‹‹መግለፃችን›› እና ‹‹ቃል መግባታችን›› አንድ ውጤት ላይ ለመድረስ መነሻ እንደሚያስፈልግ ሁሉ ወደ ተግባር ለመሸጋገርና ውጤት ለማስመዝገብ እንደ ቁጥር አንድ መነሻ ወይም መንደርደሪያ መስመር ሊቆጠር እንደሚገባ የሚያስማማን ይሆናል፡፡





ነገር ግን በመድረኮቹ ከተሳተፍን፣ ገለፃዎቹን ከሰጠንና ቃል ከገባንባቸው ቀናት ማግስት ጀምሮ ሁሌ ማስታወስንና ተግባራዊ ማድረግን የሚጠብቁ ተግባራት ፈጥጠው ይጠብቁናል፡፡

እያንዳንዳችን አለንላችሁ፣ በቃላችን መሠረት እንተገብራችኋለን፣ እንጠብቃችኋለን ብለን ከቀላሉ እስከ ወዲያኛው ጫፍ ልንዘልቅ ይገባል፡፡ ዓላማ ነውና ፡፡ ለምሳሌ ከስራ የማናረፍድ፣ የእናቴ መቀነት አደናቀፈኝ በሚል ሰበብ የማንቀር፣ ስራን ባግባቡ የምንፈጽምና የምናስፈጽም፣ ከአድሎአዊ አሠራርና ሙሰኝነት የራቀ አሰራርን የምንከተል በቢሮአችን ብዙዎች ነን፤ እንዲሁም ቃል ብቻ ገብተን የቀረንም እንደምንኖር አሌ የሚባል አይደለም፡፡ ጠብታ መርዝ ገንዳ ሙሉ ውሃን እንደሚመርዝ የሚታሰብ ሆኖ. . . . . .

ስለዚህ የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ፈፃሚዎችና አስፈፃሚዎች ከድህነት የምንላቀቅበትን ልማትንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የቃላችንን የፈፀምን ይበልጥ እየሰራን፣ የቃላችንን ያልፈፀምን ለስራችንና ለቃላችን ታማኝ በመሆን የመሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጥ መስመርን በመከተል የሚጠበቅብንን እንወጣ፡፡

**እንኳን ለገና በዓል አደረሳችሁ**



## ቢሮው የሚሰጣቸውን አገልግሎቶችና
## የሥራ ሂደቶችን ተግባራት በዌብሳይት ማሠራጨት ጀመረ።

በንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ስር የሚገኙ ዋናና ደጋፊ የሥራ ሂደቶች የሚሰጡትን አገልግሎት ቀልጣፋ፣ ጊዜና ገንዘብ ቆጣቢ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በድህረ-ገጽ ላይ ማሰራጨት መጀመሩ ተመለከተ።




ድህረ ገፁን ለመጎብኘት http//:www.snnprtradeindustry.gov.et

በኮሚኒኬሽን የሥራ ሂደት የሚዘጋጁ የህትመት ውጤቶችን ጨምሮ የእያንዳንዱ ሥራ ሂደት አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ በአማርኛና በእንግሊዝኛ መሰራጨት መጀመሩን የኮሚኒኬሽን የሥራ ሂደት ባለቤት አቶ አበበ ደንጋሞ ገልፀዋል።








በድህረ-ገጹ ላይ የሚሰራጨት መረጃዎች ተገልጋዩ የሚፈልጋቸውን መረጃዎች ባለበት ቦታ ሆኖ እንዲያገኝ ከማስቻሉም በላይ በየጊዜው ተለዋጭ የሆኑ ሁነቶች እንደሚስተካከሉ (አፕዴት እንደሚደረጉ) ያብራሩት አቶ አበበ እንቅስቃሴው የመሠረታዊ አሠራር ሂደት ለውጥ ውጤት ሲሆን ሴክተሩን በኢኮኖሚው ልማት የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት እንዲችል የሚያግዝ የማስተዋወቅ ተግባር መሆኑንም ጠቁመዋል።

በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ላሉ ለነባርና አዳዲስ ባለሀብቶች፣ ለነጋዴው ማኅበረሰብ፣ ለንግድና ትራንሥፖርት ማኅበራት፣ ለራስ ሥራ ፈጠራ ባለሀብቶች፣ በክልሉ ባሉት አጠቃላይ የንግድና የኢንቨስትመንት አማራጮችና ማበረታቻዎች ዙሪያ መረጃ የመስጠትና የማስተዋወቅ

ፋይዳ ያለው የድህረ-ገጽ ስርጭት በሴክተሩ እንቅስቃሴም ዙሪያ ማስታወቂያና ዜናዎችም የሚለቀቅበት መሆኑ ተመልክቷል፡፡

## በክልሉ ሴክተር መ/ቤቶች ለኮሚኒኬሽን የሥራ ሂደት ሠራተኞች የመሠረታዊ አሠራር ሂደት ለውጥ ስልጠና ተሰጠ፡

የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮን ጨምሮ ከተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶች ለተውጣጡ ለኮሚኒኬሽን የሥራ ሂደት ሠራተኞች የመሠረታዊ አሠራር ሂደት ለውጥ የሙሉ ትግበራ ሥልጠና በቢሮው ሚሊኒየም አዳራሽ ተሰጠ፡፡



የተከበሩ አቶ ዘሪሁን ዘውዴ

የሥልጠናውን በይፋ መጀመር በንግግር የከፈቱት በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት የመንግሥት ኮሚኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ዘሪሁን ዘውዴ የስራ ሂደቱን ሠራተኞች ሥልጠናው በየሴክተር መ/ቤቶቻቸው





የቃል አቀባይነት፣ ባለድርሻና ተገልጋይ ማህበረሰቡን የማገናኘት ሚናቸውን ለመወጣት የሚያስችላቸው መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ለስድስት ቀናት ታቅዶ የተካሄደውን በጋራ መግባባት መንፈስ በአጭር ጊዜ ለማጠናቀቅ መቻሉ ጥሩ ሂደት መሆኑን ነገር ግን ከመቼውም ጊዜ የበለጠ የላቀ ሥራ ለመስራት ተነሳሽና የአመለካከት ለውጥ ማምጣት እንደሚገባ የመንግስት ኮሚኒኬሽን ቢሮ ም/ኃላፊ አቶ ዓለሙ ዘውዴ አሳስበው ወደፊት የማብቃትና አቅም ግንባታ ሥልጠና የመስጠት ዕቅድ መኖሩንም ጠቁመዋል፡፡



የተከበሩ አቶ ዓለሙ ዘውዴ ሥልጠናውን ሲሰጡ

በሥልጠናው ሂደት የስራ ሂደቱ ፈፃሚዎች ስለሚሰጡዋቸው አገልግሎቶች እንደ ሲቪል ሰርቫንት በዓመት መስራት የሚገባቸው ሰዓታት የሥራ አፈፃፀም መለኪያና በሌሎች ፅንሰ-ሀሳቦች ዙሪያ ተገቢውን ግንዛቤ ማግኘታቸውን በሥልጠናው ማጠናቀቂ ላይ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

እመርታ ወርሀዊ መጽሔት



የሥልጠናው ተካፋዮች

በመጨረሻም የቢሮው ም/ኃላፊ አቶ ዓለሙ ቀድሞ የመንግሥት ኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ይባል የነበረው ለጊዜው የኮሚኒኬሽን የሥራ ሂደት ተብሎ መለወጡን በመግለፅ የሥልጠናውን መዝጊያ ንግግር በማድረግ አጠናቀዋል፡፡

## በክልሉ ሪፎርም ከተሞች እየተገነባ ያለው የክላስተር ግንባታ እየተጠናቀቀ ነው፡

የክልሉ መንግሥት ድህነትን ለማጥፋት እየሰራ ካለው አንኳር ነጥቦች መካከል በከተሞች ወጣቶችንና ሴቶችን በጥቃቅንና አነስተኛ ማኀበራት በማደራጀት ወደ ሥራ ማሰማራት ነው፡፡ እነኚህም ማኀበራት ያለባቸውን የማምረቻና የመሸጫ ቦታ እጥረት ለመቅረፍ ሲባል የክልሉ መንግሥት ከዞን አስተዳደሮች፣ ከከተማ አስተዳደሮችና ከማዘጋጃ ቤቶች ጋር በመቀናጀት በ22 የሪፎርም ከተሞች የክላስተር ማዕከላት ማስገንባት ከጀመረ 3 ዓመታት አስቆጥሯል፡፡ ይህም ግንባታ ከ90% በላይ እየተጠናቀቀ ይገኛል፡፡







የክላስተር ማዕከሉ ውጫዊና ውስጣዊ ገፅታ

ከሪፎርም ከተሞች መካከል ሀዋሳ፣ ዱራሜ፣ ወላይታ ሶዶ፣ ቡታጅራና ሀሰታወንዶ ከተሞች አፈፃፀማቸው ለሌሎች ከተሞች አርአያ የሚሆኑበት ደረጃ ላይ ያሉ ሲሆን ሌሎች ከተሞችም የነዚህን ከተሞች አፈፃፀም በመመልከት ግንባታውን ማፋጠን ቢችሉ ተመራጭ ይሆናል፡፡



ግንባታው ለታሰበለት ዓላማ በታሰበለት ጊዜ ያልተጠናቀቀበትን ምክንያት የክልሉ የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ም/ቢሮ ኃላፊና የኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ኃላፊ አቶ ገብረመስቀል ጫላ ሲገልፁ በነበረው የሲሚንቶና የብረታ ብረት እጥረት ምክንያት መሆኑን ገልፀው የክልሉ መንግስት የነበረበትን ድርሻ 40% በግንባታ ቁሳቁስ አቅርቦት መወጣቱን አክለዋል፡፡ በተጨማሪም በአሁኑ ሰዓት ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች የየድርሻቸውን በአብዛኛው ተወጥተዋል፡፡ ማዘጋጃ ቤቶች ላይ የሚታየውን መጠነኛ ክፍተትም ቢሆን በሚደረገው ክትትል እንደሚስተካከልና በቅርቡ ሙሉ በሙሉ ግንባታው ተጠናቆ ለማኅበራት አገልግሎት እንደሚውል አስታውቀዋል፡፡

## *ከሠሩ ይጠቀማሉ፡*

ዛሬ ዛሬ በከተሞች ስራ ፈቶ መቀመጥ እንደ አንድ ነውር መቆጠር ጀምሯል፡፡ ምክንያቱም በተከፈተው የሥራ ዕድል ዘው ብሎ ለመግባት የሚቸግሩ ውጣ ውረዶች አይታዩም፡፡ አሠራሩ ግልፅና ቀልጣፋ ከመሆኑም በላይ ለማኅበራት የአደረጃጀት፣ የብድር፣ የመስሪያና መሸጫ፣ ገበያ የማፈላለግ፣ የሥልጠና፣ የምክር፣ የጥሬ-ዕቃ፣ የተሻሻሉ መሣሪያዎችና ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት፣ የንግድ ልማት፣ የመረጃ፣ የመሰረተ ልማት አቅርቦት፣ የምርት ጥራትና ምርታማነት ማሻሻያ እና የህግ ድጋፍ አገልግሎቶች ለማናቸውም አምስትና ከዚያ በላይ በመሆን ለመደራጀትና ለመስራት ለሚመጡ ዜጎች ይሰጣሉ፡፡





ይህን ሰፊ አገልግሎት በመጠቀም እራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን የጠቀሙ ግለሰቦች አግኝተን ስናነጋግራቸው የተማከሩ ይመስል <<መንግስት በቀየሰው ፖሊሲና ስትራቴጂ መሠረት ከሰሩ የጠቀማሉ>> ሲሉ መለሱልን፡፡



የማኅበሩ አባላት በሥራ ላይ

በሀዋሳ መሀል ክፍለ-ከተማ ባለው የመስሪያ ቦታ የሀይቅ ልብስ ስፌት ማኅበር በሚል ስያሜ ተደራጅተው ከሚንቀሳቀሱት ዜጎች መካከል አቶ ጌታቸው ደምሴ አንዱ ነው፡፡ አቶ ጌታቸው በማኅበሩ ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ ተደራጅቷል፡፡ በማኅበር ከመደራጀቱ በፊት በግሉ በዚሁ ልብስ ስፌት ስራ የተሰማራው ጌታቸው እንደሚለን ከሆነ በማኅበር ተደራጅቼ መስራት ከጀመርኩ ወዲህ ጥሩ ለውጥ ለኔና ለቤተሰቤ አግኝቻለሁ ይለናል፡፡ አካል ጉዳተኝነቴም ምንም ተፅዕኖ አላደረገብኝም፡፡ ሌሎች እኔን መሰል ዜጎች ስራን ሳይመርጡ በሚቻለው ሁሉ ቢሳተፉ ውጤት

ያመጣሉ ብሎ ይመክራል፡፡ አካል ጉዳተኝነትም መስራት አይከለክልምና ከሰሩ ይጠቀማሉ ብሎናል፡፡



አቶ ጌታቸው ደምሴ

በሀይቅ ልብስ ስፌት ማኀበር በ1998 ዓ.ም 10 ሰዎች ሆነው ተደራጁ፡፡ መንግሥት ያለባቸውን የቦታ ችግር ለመቅረፍ በመሃል ከተማ በተሰራው የመስሪያ ቦታ ካለምንም ክፍያ እንዲሰሩበት ሰጣቸው፡፡ አሁን 16 አባላት ያሉት ማህበር የደንብ ልብሶችን፣ የተማሪ ዩኒፎርሞችን፣ ጋዋኖችንና ሌሎች አልባሳትን ሰርቶ ለተጠቃሚ ያቀርባል፡፡ አሁን ያላቸው ካፒታል እስከ 200 ሺ ብር ይደርሳል፡፡ በዚህ ዓመት ለመመረቅና ወደ መካከለኛ ባለሀብትነት ለመቀየር ዕቅድ አላቸው፡፡ ያሏቸው የልብስ ስፌት ማሽኖች ወደ 40 ገደማ ናቸው፡፡ ይዘታቸውም ኋላ-ቀር ነውና እንደ ሸራና ጂንስ ያሉትን ስራዎች ለመስራት አያስችሉም፡፡ በዚህም ተቸግረው ነበር፡፡ ይህም ታሪክ ሊሆን ተቃርቧል፡፡







አቶ ተካ ታቦር

የማኀበሩ ሰብሳቢ እንደገለፁልን የከተማው አስተዳደርና ሌሎች ተቀናጅተው ባደረጉት ድጋፍ UNDP ከሚባል ድርጅት በተገኘ ድጋፍ ተጨማሪ ዘመናዊ የልብስ ስፌት ማሽኖችና ቁሳቁሶች ሊገዛላቸው ቅድመ-ዝግጅቶቹ ተጠናቀዋል፡፡ ድርጅቱ ለነሱና ለሌሎች 5 ማህበራት ባደረገው 3.1 ሚሊዮን ብር የሚፈጅ ልገሳ የድርሻቸውን 308 ሺህ ብር አግኝተዋል፡፡ ልገሳውም በቁሳቁስ ላይ የሚውል በመሆኑ ቁሳቁሶቹ ሊገዙ ጨረታ ወጥቶ አሸናፊው ድርጅት ለማቅረብ ቅድመ ሁኔታዎች ተጠናቀዋል፡፡ ይህም ወደ ኢንዱስትሪያል የጋርመንት ስፌት ደረጃ እንደሚያሸጋግራቸው የማኀበሩ ሰብሳቢ አቶ ተካ ታቦር ይናገራሉ፡፡

## ለባለሀብቱ የአቅም ግንባታ ሥልጠና ተሰጠ

የቢሮው የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ዋና የሥራ ሂደት ከአራት ዞኖችና ሦስት ልዩ ወረዳዎች እንዲሁም ከአንድ ከተማ ለተውጣጡ ከ80 በላይ ለሚሆኑ ባለሀብቶች የግል ባለሀብቱ በልማቱ የጎላ ሚና መጫወት የሚያስችለውን የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም የሚያጎለብቱ ሥልጠና በቢሮው ሚሊኒየም አዳራሽ ከ20-22/4/2002 ዓ.ም ድረስ የቆየ ሥልጠና ሰጠ፡፡




የተከበሩ አቶ ታገሠ ጫፎ ሥልጠናውን በንግግር ሲከፍቱ

ሥልጠናውን በክብር እንግድነት ተገኝተው በንግግር የከፈቱት የክልሉ ምክትል ር/መስተዳድርና የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ የተከበሩ አቶ ታገሠ ጫፎ ሲሆኑ በንግግራቸውም ሥልጠናው ባለሀብቱን ያካበተውን





ልምድ ለመለዋወጥ የሚረዳው ከመሆኑም በላይ የግሉን ባለሀብት ለማነቃቃት እየተደረገ ያለውን ጥረት ያመላክታል ብለዋል፡፡ በተጨማሪም የግሉ ኢንቨስትመንት በክልሉም ሆነ በሀገሪቷ ዕድገት የማይተካ ሚና ያለው በመሆኑ ቢሮው የተመቻቸ አሠራር ለባለሀብቱ ለማቅረብ የተቻለውን ጥረት ሁሉ ያደርጋል በማለት ባለሀብቱ በሚሰጠው ሥልጠና ንቁ ተሳትፎ እንዲያደረግ አሳስበዋል፡፡




ባለሀብቶቹ ሥልጠናውን በቡድንና በአጠቃላይ ሲካፈሉ

በዚህ ስልጠና ከደቡብ ኦሞ፣ ጌዲኦ፣ ሲዳማ፣ ስልጢ ዞኖች፣ ከሀዋሳ ከተማና ከሀላባ፣ አማሮና ቡርጂ ልዩ ወረዳዎች የተውጣጡ ባለሀብቶች ሲገኙ በተጨማሪም የሥራሂደቱ አስተባባሪዎችና የሚመለከታቸው ሃላፊዎችም ተገኝተዋል፡፡

ሥልጠናውም በሥራ ሂደቱ ባለቤት፣ በሥራ ሂደቱ ባለሙያዎችና ከፌደራል በተጋበዙ እንግዶች በኢንተርፕሩነርሽፕ፣ በንግድ ሥራ አመራር፣ በግብይትና ሽያጭ ስልት፣ በንግድ ዕቅድ አፃፃፍ ቴክኒክና ሌሎች ርዕሶች ላይ አሳታፊ በሆነ መልኩ ተሰጥቷል፡፡

# ጠቅላላ ዕውቀት፡

መንደር በሆነው ዓለማችን ያለ ይቅርታ መኖር እንደማይቻል ያውቃሉ?

በፈጣሪያችን ቅዱስ ቃል <<የምታየውንና አጠገብህ ያለውን ወንድምህን ይቅር ሳትል ይቅርታን እንዴት ታገኛለህ?>> ተብሎ ተጽፏል፡፡ በየትኛውም እምነትና ሃይማኖት ይቅርታና ይቅር ባይነት በተለያዩ ቃላት ይገለፃሉ፡፡ የሥነ-ልቦና ጠበብቶች የይቅርታን አስፈላጊነት ብቻ ሳይሆን ያለ እሱ ሰው ሆኖ ከሰው ጋር መኖር አስቸጋሪ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ በአጭሩ እንደሚከተለው ያዘጋጀነው ጽሁፍ ምንጭ <<Personal Growth And Behavior>> የተሰኘው መጽሐፍ ነውና እነሆ፡፡

⇨ **ስኬታማ ይቅርታ ሁለት ቁልፍ ነገሮች አሉት፡**

1. የተፈፀመው ስህተት ግንኙነትን የሚጎዳ መሆኑን መቀበል፡ መልካም ግንኙነት የሚያበላሽ ስህተት መፈፀምን በማመን ለተፈጠረው ነገር ኃላፊነትን መውሰድ ወደ አንድነት የሚያመጣ የስልጣኔ ምልክት ነው፣

2. ያን ስህተት ለምን እንደፈፀሙ በሚገባ ማብራራት፡ አሳማኝ፣ ቅንና ትክክለኛ ምክንያትና መንስዔ ለተፈፀመው ስህተት ማብራራት መቻል ይቅርታን ስኬታማ ያደርገዋል፡፡ እንደዚያ ማብራራት ጥፋቱን ሆን ተብሎ አቅዶና ተዘጋጅተውበት አለማድረግን ስለሚገልጽ በጥፋቱ የሚያምኑበት አለመሆኑን ስለሚያመለክት ይቅርታን የተሳካ ያደርገዋል፡፡





⇨ **ይቅርታ ለምን ያስፈልጋል?**

የይቅርታ አስፈላጊነት የመስኩ ተመራማሪዎች እንደሚያብራሩት በአራት መልኩ ሊገለጽ ይችላል፡፡

1. ግንኙነትን ወደቀድሞው ሁኔታ ለመመለስ፣
2. የተፈጠረው ስህተት ሌላውን ወገን የሚጎዳ ሆኖ በመገኘቱ ፈፃሚው አዘኔታውን ለመቀነስና ህመሙን ለመጋራት፣
3. አንዳንዶች በፈፀሙት ስህተት ከቅጣት ለማምለጥ እና
4. ሌሎች የራሳቸውን ህሊና ከጥፋተኝነት ነፃ ለማድረግ ናቸው፡፡

ሳይኮሎጂስቶች እንደሚሉት የስኬታማና ትክክለኛ የይቅርታ መንስዔዎች የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ሲሆኑ ቀሪዎቹ ሁለቱ ከራስ ፍላጎት (ከበዳዩ) እንጂ ከተበዳዩ አንፃር ያን ያህል ፋይዳ የለውም፡፡ ያም ሆነ ይህ ለጤናማ ማኅበራዊ ግንኙነት፣ ለደስተኛ የቤተሰብ ህይወት እና ለውጤታማ የሥራ አካባቢን ለመፍጠር ሁላችንም ይቅርታ ለማድረግ የለሰለሰ ልብ ይቅር ለማለትም የተዘጋጀ አዕምሮ ይኑረን እንላለን፡፡

**The best teachers will not give you some thing to drink, they will make you thirsty.**

(For positive thinking)



## ለ ፈ ገ ግ ታ፡

# ‹‹ እንደዚያ ከሆነማ . . . . ››

አባት፡ የመረጥኩልህን ልጃገረድ እንድታገባ እፈልጋለሁ?

ልጅ፡ የትዳር ጓደኛዬን ራሴ መርጣለሁ፡

አባት፡ ነገር ግን ልጅቷ የቢልጌት ናት'ኮ?

ልጅ፡ መልካም. . . ነገሩ እንደዚያ ከሆነ . . . ብሎ

ሲመልስለት በሚቀጥለው አባት ወደ ቢልጌትጋ ይሄድና

አባት፡ ለልጅህ ባል አግኝቼላታለሁ?

ቢልጌት፡ ልጄ ለትዳር አልደረሰችም፡

አባት፡ ነገር ግን ይህ አፍላ ወጣት ልጅኮ የዓለም ባንክ ፕሬዚዳንት ነው?

ቢልጌት፡ አሃ. . . ነገሩ እንደዚያ ከሆነ. . . . .

ከዚያ በኋላ አባት ወደ ዓለም ባንክ ፕሬዚዳንት ይሄድና የሚከተለውን ይለዋል።

አባት፡ ወጣት ልጅ ለምክትል ፕሬዚዳንትነት የተጠቆመ ልጅ አለ?

ፕሬዚዳንቱ፡ከምፈልገው በላይ ብዙ ም/ፕሬዚዳንቶች አሉኝ፡

አባት፡ ነገር ግን ይህ ወጣት የቢልጌት ልጅ ባል ነው'ኮ?

ፕሬዚዳንት፡አሃ. . . . እንደዚያ ከሆነ . . . . . ።

በመጨረሻም አባት ልጃቸውን ጠሩና ‹‹ቢዝነስ የሚሰራው እንደዚህ ነው›› ብለው ነገሩት።





